# በምስራቅ ወለጋ ዞን አንድ የአማራ ወጣት ባለሀብት በኦሮሚያ ልዩ ኃይል በጥይት ተገደለ

February 16, 2021

የካቲት 7 ቀን 2013 በሊሙ ወረዳ አርቁንቢ ቀበሌ አማራዎች ሰርግ ላይ በነበሩበት ወቅት ወደ አካባቢው ያቀኑና በኦነግ መመታት የተበሳጩ የኦሮሚያ ልዩ ሀይል አባላት በር እየሰበሩ ግድያ፣ የጦር መሳሪያ ንጥቂያና ዝርፊያም መፈፀማቸው ይታወቃል።

በዚህም 5 አማራዎችና 1 የጉምዝ ተወላጅ የተገደሉ መሆናቸውን አሚማ ምንጮችን ዋቢ በማድረግ መዘገቡ ይታወሳል።

ወደ አካባቢው መከላከያ መግባቱ ቢነገርም ቁጥሩ አነስተኛ በመሆኑና ልዩ ኃይሉ ከአካባቢው ባለመውጣቱ ከፍተኛ ስጋት እንደነበርና ይህን ተከትሎም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ ከቀዬው እየለቀቀ መውጣቱ ተሰምቷል።

በዛሬው እለት የካቲት 9 ቀን 2013 የኦሮሚያ የልዩ ኃይል አባላት በአንቡላንስ እየተንቀሳቀሱ "ኑ ተሰብሰቡ፣ ሰላም ነው፣ እንወያይ" በማለት ሲቀሰቅሱ ማርፈዳቸውን ነው ነዋሪዎች የገለፁት።

በጥቃቱ ምክንያት ከመንደር 10 ሸሽቶ ወደ መንደር 9 በማቅናት ከቤተሰቦቹ ጋር የቆየው ወጣቱ ባለሀብት ዋሴ በላይ ሰላም ከሆነ በሚል ወደ መኖሪያ ቤቱ ሲመለስ ከአንቡላንስ ካሉት አንደኛው የልዩ ሀይሉ ኃላፊ በመውረድ አስቁሞ የት ነበርክ በሚል እንደጠየቀው ምንጮች ተናግረዋል።

ከዛም ጥሮ ግሮ መኪና በመግዛት በሆቴል ስራ የተሰማራውን ወጣት ዋሴን የራሱን መጠበቂያ ሽጉጥ ከተቀበለ በኋላ ተኩሶ እንደገደለው ከስፍራው የነበሩ ምንጯችን ለአሚማ ገልፀዋል።

ዛሬ ፍፁም ሰላማዊ የሆነ ለአማራ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ጠበቃ የሆነ ንፁህ ሰው በልዩ ኃይሎች ኃላፊ እንደተነጠቁ ነው በሀዘን ስሜት ያስታወቁት።

አስከሬኑን ወደ ቤተሰብ ለማድረስም መኪና ባለመገኘቱ እንደተቸገሩ ጭምር ተነግሯል። ለማጣራት ባይችሉም ተጨማሪ አንድ አማራ ሳይገደል እንዳልቀረም ሰምተናል ብለዋል።

የአካባቢው ነዋሪዎች በገበሬዎች ላይ ግድያ እየፈፀመ ያለው የኦሮሚያ ልዩ ኃይል ሙሉ በሙሉ ወጥቶ በመከላከያ ሰራዊት እንዲተካላቸው ጠይቀዋል።

አሚማ የተጣራ ተጨማሪ መረጃ እንዳገኘ ወደ እናንተ የሚያደርስ ይሆናል።

ምንጭ: አማራ ሚዲያ ማዕከል/አሚማ